**Ethiopian Journal of Business and Social Science**

**DOI:** https://doi.org/10.59122/205F55to

**Volume: 8 Number: 2, 2025, Pages: 62- 82**

**ISSN: 2707-2770**

# የጋሞ ዱቡሻ ዎጋ ሚና ግጭትን ከመከላከልና ዘላቂ ሰላም ከማፅናት አንጻር

**ሰዒድ አህመድ[1]*፡ በሻ በምቤ[1]፡ተመስገን ምንዋጋው[1]፡ ወንድይፍራው ከተማ[2]፡ አረጋ አሸናፊ[2]፡ ታሪኩ ኦይቻ[3]፡ ሙሉነህ ተፈራ[3]፡ እና ተስፋዬዮን ዮሴፍ[4]**

***Article Info***

*Accepted on:*

*June, 2025*

*Published on:*

*October, 2025*

***©Arba Minch University, all rights reserved***

***አጽህሮተ ፅሁፍ***

*ኢትዮጵያ የበርካታ ብዝሃ-ባህልና አገር በቀል ዕሴቶች ባለቤት ከመሆኗም በላይ እነዚህ ተቋማት ከጥንት ጀምሮ የህዝቦችን አንድነትና ዘላቂ ሰላምን በማስፈን አይነተኛ ሚና እየተጫወቱ ከዘመን ዘመን ለመሸጋገር ችለዋል፡፡ ከነዚህም አንዱ የጋሞ ዱቡሻ ዎጋ ሲሆን ይህ ጥናት የሚያተኩረው የጋሞ ዱቡሻ ዎጋ እንደ አንድ አገር በቀል ባህላዊ ዕሴት ለዘላቂ ሰላም ግንባታ ያለው ፋይዳ ይመረምራል፡፡ ዱቡሻ ዎጋ የጋሞ ማህበረሰብ ቀዳማይ(ባይራ) የእምነትና የባህል ተቋም ከመሆኑም በላይ ጥልቅ ፍልስፍናና ንጽረተ-ዓለም የሚታይበት ፈርጀ ብዙ ተቋም ነው፡፡ ከነዚህም መካከል በተለይ ዱቡሻ ዎጋ የሚታወቀው ግጭትን በመከላከልና ዘላቂ ሰላምን በማስፈንና የህዝቦችን አንድነት በማጠናከር ላይ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ሁሉንም የጋሞ ዴሬዎችን በማካተት ሃምሳ ሰዎች መረጃ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ ለጥናቱ ዓይነታዊ የጥናት ዘዴን የተጠቀምን ሲሆን የቁልፍ ቃለ መጠይቅ፣ አትኩሮት የቡድን ዉይይትና ምልከታ በማድረግ የተሰበሰበውን መረጃ ከአጋዥ ፅሁፍ ጋር ክለሳ በማድረግ ዉጤቱን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ የጥናቱ ዉጤት እንደሚያሳየው የጋሞ ማህበረሰብ ዱቡሻ ዎጋን ከጥንት ጀምሮ በእለት ተእለት ኑሮው ሲገለገልበትና ሰላም ሲያስጠብቅበት እስከአሁን ድረስ ሊዘልቅ ከመቻሉም ባለፈ የጋሞን አንድነት በማጠናከር ብሎም የጋሞ ህዝብን ሰላም ወዳድነት በተግባር ያሳየ ድንቅ አገር በቀል እሴት እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ዱቡሻ ዎጋና ሌሎች ተመሳሳይ ዕሴቶች ካላቸው ማህበራዊ ቅቡልነትና ተደራሽነት አንጻር ለአገራዊ ዘላቂ ሰላም ግንባታ መጠቀም ቢቻል ፋይዳቸው የጎላ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር እነዚህ ዕሴቶችን ከዘመናዊ አሰራር ጋር ማቀናጀት ቢቻል የህብረተሰቡን ጊዜና ገንዘብ በመቆጠብ፤ ቁርሾን ከልብ በማውጣት ብሎም የቀደመውን ማህበራዊ መስተጋብርን በማደስ፤ ወቅታዊ ቀውሶች በማስቀረት፣ ዘላቂ ሰላም እንዲገነባ ዓይነተኛ ሚና ከመጫወት አልፈው ለአገራዊ ሰላምና ብልጽግና ፋይዳቸው ከፍተኛ ስለመሆኑ ዱቡሻ ዎጋን እንደ ማሳያነት ቀርቧል፡፡*

*ቁልፍ ቃላት፡-* ዱቡሻ ዎጋ፤ አገር በቀል ዕሴት፤ ጋሞ፤ ኢትዮጵያ

[1] ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ
[2] ከጋሞ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ
[3] ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ
[4] ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን
*** Corresponding author: E-mail addresses:** seid.ahmed@amu.edu.et

## መግቢያ

የጋሞ ዱቡሻ ዎጋ[5] የሁለት ቃላት ጥምረት ሲሆን ዱቡሻ ማለት በጋሞ ሰፊ የሆነ የህዝብ መሰብሰቢያ ቦታ ሆኖ በርካታ ከበራዎች የሚከኑበት ቦታ ሲሆን ዎጋ ደግሞ ስርዓት ወይም ማህበራዊ ህግ/ወግ የሚል ትርጓሜ ኖሮት ህጎቹ ተፈፃሚ የሚሆኑት ደግሞ በዱቡሻ ላይ ብቻ በመሆኑ እንደአንድ የጋሞ አገርበቀል ተቋም የሚወሰድ ነው፡ ፡ ስለሆነም የዚህ ጥናት ዋና አላማም የጋሞ ብሔረሰብ ስለዱቡሻ ዎጋ ያለውን ጥልቅ እሳቤ፣ እምነትና አተያይ ብሎም ዱቡሻ ዎጋ በጋሞ ማህበረሰብ ያለዉን ቅቡልነት እንደ አንድ የአገር በቀል ተቋም/ስርዓት ለማሳየትና ዕሴቱ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን በሚጫወተው ሚና ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

የጋሞ ዱቡሻ ዎጋ ጽንሰ-ሐሳብን ለመረዳት በቅድሚያ በዓለም ዙሪያ ስለ ‹ቅዱስ ስፍራዎች› የተደረጉ ጥናቶችን ዳሰሳና ንፅፅር በማድረግ መዳሰስ አስፈላጊነቱ የጎላ ነው፡፡ ጥናቶቹ እንደሚያመለክቱት በዓለም ላይ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን የማህበረሰቡን ዕሴቶች የሚያጠነጥኑት በማህበረሰቡ ዘንድ ‹በተፈጥሮ ቅዱስ› (sacred) ተደርገው በሚወሰዱና በሚታመኑባቸው ስፍራዎች ጋር የተዛመዱ እንደሆኑ ይገልጻሉ (Schaaf, 2003) ፡፡ እነዚህ ስፍራዎች ለሰው ልጆች እጅግ አስፈላጊ ለሆነው ለዘላቂ ሰላምና ልማት ዋና መሠረት ከመሆናቸውም በላይ በህብረተሰቡ ዘንድ በእጅጉ ይከበራሉ፤ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓቶችና ከበራዎችም ይከወንባቸዋል (Adam, 2012; Desalegn, 2007) ፡፡

‹ቅዱስ ስፍራዎች› (sacred places) በህብረተሰቡ ዘንድ እጅግ የሚፈሩና የሚከበሩ ተፈጥሮአዊ ቦታዎች ስለሆኑና እውነትን ብቻ የሚነገርባቸው በመሆናቸው በህብረተሰቡ ዘንድ ቅቡልነታቸው የጎላ እንደሆነ መረጃዎች ያስገነዝባሉ (Adam, 2012; Desalegn, 2007)፡፡ በዓለም ላይ በርካታ የተፈጥሮ ቦታዎች እንደ ‹‹ቅዱስ ስፍራ›› ተደርገው ከሚወሰዱት መካከል ለአብነት ለመጠቀስ ካስፈለገ የፉጂ ተራሮች ለጃፓኖች፤ የሜሩ ተራሮችን ደግሞ በህንዶች ዘንድ ያላቸውን ቦታ መጥቀስ ይቻላል (Eller, 2007; Iwatsuki, 2003)፡፡

[5] ይህ ጥናት “ዱቡሻና የዱቡሻ ዎጋ በጋሞ ማህበረሰብ” የሚል ርዕስ እየተሰራ የሚገኝ የጥናት ፕሮጀክት አካል ሲሆን ጥናቱን የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፤ ከጋሞ ዞን አስተዳደር፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ቢሮና ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ጋር በትብብር የጋሞ ዱቡሻ ዎጋን በዩኔስኮ በማይዳሰስ የሰው ልጅ ወካይ ቅርስነት ለማስመዝገብ እየተሰራ ባለው ጥናት የተሰራ ሲሆን የፅሁፉ አቅራቢዎቹም የጥናት ቡድኑ አባል ናቸው፡፡ ለዚህ ስራ መሳካት አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ እያደረገ ስላለው ድጋፍና ክትትል ልባዊ ምስጋናችንን ለማቅረብ እንወዳለን፡፡

በአህጉራችን አፍሪቃም በርካታ አፍሪቃዊ ‹ቅዱስ› ስፍራዎች ስለመኖራቸው ነቃሽ መጥቀስ አያስፈልግም። ይኸውም አፍሪቃዊያን ከተፈጥሮ ጋር ባላቸው ጥብቅ መስተጋብርና የዕለት ተዕለት ቁርኝት ብሎም መንፈሳዊና ባህላዊ ህይወታቸቸው ከተፈጥሮ ጋር የተሳሰረ በመሆኑ በርካታ የተፈጥሮ ቦታዎችን (በተለይም ተራሮች፤ ወንዞች፤ ጥብቅ ደኖች ወዘተ) እንደ ቅዱስ ስፍራዎች አድርገው ይወስዳሉ። እነዚህ ‹ቅዱስ› ተብለው የሚታመኑባቸው ቦታዎች በህብረተሰቡ ዘንድ በእጅጉ ይፈራሉ፤ ይከበራሉም። መንፈሳዊና ባህላዊ ከበራዎች ይከወንባቸዋል። እነዚህ ስፍራዎች የእምነትና የንጽረተ ዓለም እሳቤ ምንጭ ከመሆናቸው ባሻገር የህብረተሰቡን ማህበራዊና ፖለቲካዊ መስተጋብር በመምራት፤ የተዛነፈውን በማረቅ/በማስተካከል የህዝቡን የዕለተ ተዕለት ዉሎውን የተሳለጠና ሰላማዊ ይሆን ዘንድ ከፍተኛ ሚና በመጫወት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገሩ አሁን ድረስ የማይተካ ሚና በመወጣት ላይ ይገኛሉ(Adam, 2012; Desalegn, 2007)።

በኢትዮጵያ በተለይም በደቡብና በደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች በርካታ እንደ ቅዱስ የሚያወስዷቸውና በአካባቢው ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ የሚያደርግላቸው በርካታ ቦታዎች መኖራቸውን መረጃዎች ያሳያሉ። በተለይም ኦዳ በኦሮሞ፤ የዎኖሸ ቅዱስ ቦታ በሲዳማ፣ የሸካ ጥብቅ ደን በሸካ፣ የጋሞ ዱቡሻ ዎጋ በጋሞ እና ሌሎች በርካታ ቅዱስ የተባሉ ቦታዎችን ለአብነት መጥቅስ ይቻላል (Booker & Shrumm, 2012; Desalegn & Healey, 2012; Freeman, 1999; Zerihun, 2014)።

በተለይም ‹ቅዱስ ስፍራዎች› (sacred places) የአንድ ማህበረሰብ አገር በቀል ዕውቀትና ዕሳቤ፤ እምነትና ፍልስፍና፣ ባህልና ታሪክ፤ ብሎም ማህበረሰባዊ መስተጋብርና ዘላቂ ሰላምን የሚያሳልጡ በመሆናቸው በህብረተሰቡ ዘንድ ከበሬታቸውና ቅቡልነታቸው የጎላ በመሆኑ፤ ከነዚህም መካከል ይህ ፅኁፍ በዋናነት የጋሞ ዱቡሻ ዎጋ ስርአት በጋሞ ማህበረሰብ ዘንድ እንደ‹ቅዱስ ስፍራ› ተደርጎ ስለሚወሰድ ጥናቱ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይመረምራል። በመሆኑም ይህ ዕሳቤ ሰፋ ያለ ትርጉም ያለው መሆኑን ደስታ የተባለው ተመራማሪ እንደሚከተለው ይገልፃል።

> For Gamo the term "sacred" is anchored in their cosmology, their belief system and their local customary admistrative philosophy. The term "sacred" (*boncho bessa*) literally means to show special respect, venerate and honor to creator, things, places and people that are highly valued and respected ( Desta, 2024).

ከዚህ በተጨማሪም በጋሞ ላይ ሰፋ ያለ ጥናት የሰራው ታደሰ ወልዴ የጋሞ ማህበረሰብ ዱቡሻ ዎጋን በአለም ላይ ካሉ ቅዱስ ስፍራዎች አንዱ መሆኑን ሲያብራራ፡-

> … ፈጣሪ ሰውንና ተፈጥሮን ፈጠረ፡፡ከተፈጥሮ የተወሰኑትን የመሬት ክፍሎች እግዚአብሔር ቅዱስ አድርጎ ለያቸው ምክንያቱም ሰዎች እግዚአብሔርንና የተፈጥሮን መንፈስ እንዲያከብሩ እና እንዲፈሩ ለማድረግ በማሰብ ነው፡፡ በመሆኑም በጋሞ ቅዱስ የሚለው ሐሳብ የተሰረጸው *በነ ወጋ ወይም ዎንታ ወጋ* በሚለው በማህበረሰቡ ጥንታዊ ሃይማኖት ሥርዓት ውስጥ ነው፡፡ በጋሞ *በነ ዎጋ ወይም ዎንታ ዎጋ* እምነት ከመለኮት ጋር የተገናኘ ሲሆን ይህም በሰማይ የሚኖር እግዚአብሔርን ወይም ደግሞ በምድር የሚኖር የተፈጥሮ ወይም በመሬት የሚኖሩ መናፍስትን ጭምር ያካትታል (ታደሰ፣ 2009)፡፡

ምሁሩ ‹‹በመሬት የሚኖሩ መናፍስት›› የሚለውን ዕሳቤ ሲያብራራ ‹‹የዘር ሐረግ መናፍስት (ancestral spirits) እና የተፈጥሮ መናፍስት (spirits of nature) የሚይዝ ሲሆን ሁለቱም በመሬት የሚኖሩና የሰዎችን እሳቤንና የእለት ተዕለት ኑሮአቸውን የሚቀርፁ ናቸው›› በማለት ይገልጻል፡፡ በመሆኑም ጋሞ በሰማይ እግዚአብሔርን በምድር ‹የተፈጥሮ መንፈስ ያረፈባቸውን› የተለያዩ የተፈጥሮ ቦታዎችን (ዱቡሻ፣ ባሌ፣ ካሻ (ጥብቅ ደኖች)[6]፣ ተራሮችን በእጅጉ ይፈራል፤ ያከብራልም (Desalegn, 2007; Freeman, 1999)፡፡

በተለይም ዱቡሻ ዎጋን እንደ ‹ቅዱስ› ተደርጎ እንዲታመን ከሚያደርገው ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ በዱቡሻ ላይ በርካታ ያልተፃፉ ህጎች (ዎጋ) የሚተገበሩበት ከመሆኑም በላይ ህጎቹን መተላለፍ በባህሉ ከፈጣሪ ቁጣ ወይም ጎሜ (መቅሰፍት) ያስከትላል ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ያስረዳሉ፡፡ ይህንንም የዱቡሻን ጥልቅ እምነትና ‹ቅዱስነት› አንድ የጋሞ አባት ሲገልፁ፡

> …አንድ ሰው ዱቡሻ ላይ ሲቆም/ሲወጣ በረሃ ላይ ሆኖ ከበረዶ የበለጠ አጥንቱ ስር ገብቶ ይቀዘቅዘዋል/ያንቀጠቅጠዋል፤ በረዶ ላይ ቆሞ በረሃ ላይ እንዳለ ሰው በሙቀት ያቃጥለዋል/ላብ ያሰምጠዋል፡፡ ምክንያቱም ያ ቦታ ፍጹም እውነትና እውነት ብቻ እንዲነገር ፈጣሪ ለሰው ልጅ ያዘጋጀው ቅዱስ ስፍራ ተደርጎ ስለሚወሰድና ይህንን መተላለፍ ከፈጣሪ ቁጣ ወይም መቅሰፍት (ጎሜ) ሊያስከትል ስለሚችል ነው፡፡

[6] ለምሳሌ ታዋቂው ዶርቦ ዱቡሻ በጎኑ የናጋሳ ጥብቅ ደን ሲገኝ በአሻጋሪው የብርብርና የበረዳ ገዳሞች ይገኛሉ፡፡

በጋሞ ማህበረሰብ ዘንድ ጎሜን ያስከትላሉ ተብለው ከሚታሙኑ በርካታ ባህላዊ ክልከላዎች እንዳሉ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ። ከነዚህ ክልከላዎች መካከል በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል የህብረተሰቡን ሰላማዊ የህይወት መስተጋብር ማወክ፤ ሴትን መድፈር፤ መዋሸትና በሀሰት መማል፤ ድንበር መግፋት፤ መስረቅ፤ መዝረፍ፤ ንብረትን አላግባብ ማባከን፤ ነፍስ ማጥፋት (የእንስሳትንም ቢሆን)፤ ዝሙት፤ ስንፍናና ልመና፤ ስልጣንን አላግባብ መጠቀምና ድሀን መበደል፤ የባህላዊ ሹማምንትም ስርዓቱ ከሚፈቅደው ዉጭ ህጉን አለማክበርና አለማስከበር፤ በህብረት ስራ አለመሳተፍ፤ አለመረዳዳትና አለመተጋገዝ፤ ታናሽ ታላቅን አለማክበር፤ የህዝብ ዉሳኔን አለመቀበል፤ የኑዛዜ ቃል አለማክበር፤ እና ሌሎችንም ያጠቃልላል። እነዚህን ክልከላዎች መተላለፍና በዱቡሻ ላይ መካድ ጎሜን (መቅፀፍትን) ያስከትላል ተብሎ ይታመናል። መቅሰፍቱም ከትውልድ ወደትውልድ ሊሸጋገር ይችላል ተብሎ ስለሚታመን የጎሜ የመንጻት ስርዓት (ጎሜ ጌሽ) በመፈፀም ወደስርአቱ በመግባትና ራስን ለህጎቹ በማስገዛት ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ከማድረጉም በላይ በህበረተሰቡ ዘንድ ቅቡልነቱ የጎላ በመሆኑ እንደእምነት ሊወሰድ ተችሏል። በሌላ አገላለፅ የዱቡሻ ዎጋ ክልከላዎችን ፈጣሪ ለህዝቡ ያወረደውና እንደ እምነት አድርገው የሚቆጥሩት ዋናው የጋሞ አገር በቀል ዕምነት/ስርዓት በመሆኑ የጋሞ ዱቡሻ ዎጋን እንደ‹ቅዱስ ስፍራ› የሚወሰድበት ሌላኛው አመክንዮ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም ጋሞ እስከአሁን ድረስ የራሱን የአገር በቀል ዕሴት በሆነው በጋሞ ዱቡሻ ዎጋ ግጭቶችን እያስወገደ ሰላሙን በዘላቂነት በማስጠበቅ ከራሱ አልፎ ለሌሎች አርአያነት ያለው ተግባር በማሳየቱ ለዚህና ለሌሎች የአገር በቀል እሴቶች ልዩ ትኩረት መስጠት ቢቻል የአገራችንን ችግር በራሳችን አገር በቀል ዕውቀትና ዕሳቤ መፍታት የምንችል ጠንካራ ህዝቦች መሆናችንን የሚያሳይ በመሆኑ ይህንን ጥናት እንደማሳያ ሊወሰድ ይችላል።

## የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በመስከረም 2010 ዓ.ም የሽግግር ወቅት በመሃል አገር[7] በተፈጠረ ችግር ስሜታቸው የተነካና በሁኔታው ያዘኑ የጋሞ ወጣቶች በአርባ ምንጭ ከተማ መሃል ላይ በሚገኘው የጋሞ አደባባይ ተሰባስበው በከተማው በሚገኙ ህዝባዊና ሌሎች ተቋማት ላይ ጥፋት ለመፈፀም በተሰባሰቡበት ቅፅበት በአካባቢው ሲጓዙ የነበሩ የጋሞ አባቶች እርጥብ ሳር በጥሰው ወደላይ በማድረግና በመንበርከክ፤ እናቶች ተንበርክከው መቀነታቸውን

[7] በወቅቱ በአዲስ አበባ ከተማ በቡራዩ አካባቢ በጋሞ ተወላጆች ላይ ችግር ተፈጥሮ ነበር።

በመፍታትና ጡታችን በመያዝ የወጣቶችን የጋለ ስሜት ሲያበርዱ በቦታው የዚህ ፅኁፍ አቅራቢዎች ለመታዘብ በመቻላቸው ለዚህ ጥናት ዋነኛ መነሻ ሊሆን ችሏል፡፡

በወቅቱ ወጣቶችም የጋሞ አባቶችና እናቶች በዱቡሻ ዎጋ መሰረት በእጃቸው የያዙት የተበጠሰ ዕርጥብ ሳርና መንበርከክ ብሎም የእናቶች ድርጊት ትርጉሙ ገዝቷቸው፤ በደላቸውን ለፈጣሪያቸው ሰጥተው፤ ስሜታቸውን ያበረደበት እሳቤ ለዚህ ጥናት ሌላውና ዋነኛው አነሳሽ ምክንያት ሊሆን ችሏል፡፡ ህዝቡ በተለይም ወጣቱ በጋሞ ህዝብ ዘንድ ትልቅ ቦታ ላለው ባህልና እንደቅዱስ ለሚወሰደው የጋሞ ዱቡሻ ዎጋ ምንነትና አረዳድ፤ ለዘመን አመጣሽ እሳቤ አለመንበርከኩና እሴቱ በመጠቀም ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ማድረጉ ለአካባቢው ህዝብ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ትልቅ ትርጉም ያለው በመሆኑ በጋሞ ዱቡሻ ዎጋ ላይ ጥልቅ ምርምር ብናደርግ ፋይዳው ሰፊ መሆኑን በመረዳት የተጀመረ ስራ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር የነደደ እሳትን እርጥብ ሳር በጥሶ ቂም በቀልን ማጥፋት የሚችል ተቋም ያለን ህዝቦች መሆናችን ብቻ ሳይሆን፤ ወጣቶችም ጎሜን መፍራታቸውና ባህላቸውን ማክበራቸው ይህ ባህል ለሚቀጥለው ትውልድ መሸጋገር እንዲችል ጥናቱን ለመጀመር አነሳስቶናል፡፡



ስዕል.1

በመስከረም 2010 ዓ.ም በአርባ ምንጭ ከተማ ጋሞ አደባባይ ላይ አባቶች ሳር በጥሰው በመንበርከክ ግጭት ሲያበርዱ የሚያሳይ

በተመሰሳይ ወቅት በጋሞ ዞን ከካምባ ወረዳ በተነሳው የመዋቅር ጥያቄ ጋር ተያይዞ በካምባ ከተማ ላይ ችግር ሲፈጠር የከተማው ወጣቶች ከበቀል ይልቅ ወደ ባህላቸው በመመለከት በዱቡሻ ዎጋ ስርአት ሰላም እንዲፈጠር ማድረጋቸው ለዚህ ጽሑፍ መነሻ ሊሆን ችሏል፡፡ በአጠቃላይ የጋሞ ዱቡሻ ዎጋ በጋሞ ማኅበረሰብ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ብቻ ሳይሆን በአገራችን የሚገኙ በርካታ የአገር በቀል ዕውቀቶችና ተቋማት ያላቸውን ዘመን ተሸጋሪና ሳይበረዝና ሳይከለስ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገር የኖረ ጠንካራ ባህል መሆኑን ለማጥናት የተደረገ ሲሆን ይህን ስራ ለመስራት በወቅቱና በአጋጣሚ በቦታው ለመታዘብ የተቻለ ሲሆን በዚህ መነሻነት የጋሞ ዱቡሻ ዎጋንና ሌሎች የሀገር በቀል የግጭት መከላከያ መንገዶችን ማጥናት ፋይዳቸው የጎላ በመሆኑ ይህን ጥናት ለማጥናት እንደአንድ አነሳሽ ምክንያት ሊወሰድ ይችላል፡፡





ስዕል.2

የካምባና ጋርዳማርታ ሽማግሌዎች በሊሻ ወንዝ ላይ እርቅ ሲፈፀሙ የሚያሳይ (ከካማባ ወረዳ የተገኘ)

## የጥናቱ ዘዴ

የአንድ ማህበረሰብን እሳቤ፣ እምነት፣ ፍልስፍና፣ የእለት ተእለት መስተጋብሮችን ማለትም ማህበራዊ ግኙኙነት፣ ተግባቦትና ዘላቂ ሰላም ግንባታ ላይ ዱቡሻ ዎጋ ያለውን ሚና ለማጥናት ዓይነታዊ የጥናት ዘዴ (qualitative method) የተሻለ በመሆኑና መረጃዎቹን ለመተንተን መጠናዊ ጥናታዊ ዘዴ(quantitative method) ለመግለጽ አዳጋች በመሆኑ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅመናል፡፡ ጥናቱ የተካሄደው ሁሉንም የጋሞ ዞን ወረዳዎችን (በተለምዶ ደሬዎች) በማካተት ከየካቲት እስከ ግንቦት 2016 ዓ.ም ዉስጥ ነው፡፡ መረጃ ለመሰብሰብም የቁልፍ ቃለ መጠየቅና የትኩረት የቡድን ውይይትን በመጠቀም ሲሆን በአጠቃላይ ሁሉንም ደሬዎች ባካተተ መልኩ ሃምሳ መረጃ ሰጪዎች በጥናቱ ተሳትፈዋል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ ዱቡሻዎች ላይ ህዝቡ ግጭቶችንና አለመግባባቶችን ሲፈታ በአካል በመገኘት ሂደቶችን ቀጥተኛ ያልሆነ

ተሳትፎና ምልከታ ለማድረግ ችለናል። የተሰበሰበውንም መረጃ ከተለያዩ የፅኁፍ መረጃዎች ጋር ክለሳ በማድረግ ለመተንተን ተሞክሯል::

**የጋሞ ዱቡሻ ዎጋ በጋሞ ማህበረሰብ እይታ**

የጋሞ ዞን በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኝ ሲሆን በተለምዶ የጋሞ ሰንሰላታማ ተራሮች አካባቢ በመባል የሚታወቅና የበርካታ ተፋሰሶች መነሻና የአባያና ጫሞ ሀይቆች መገኛ እንደሆነ ጸኃፊዎች ይገልፁታል (ፍሪማን 2004)። የጋሞ ህዝብ እኤአ በ2007 በተካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራ 1.5 ሚሊዮን ህዝብ በላይ እንደሚሆን ይገመታል። ቋንቋውም በኦሟዊ ቋንቋ ቤተሰብ አባል የሆነው የጋሞኛ ቋንቋ ተናጋሪና ከጥንት ጀምሮ እንስሳትንና ተክሎችን በማላመድ ብሎም እርሻን በመጀመር ከሚጠቀሱት ቀደምት ህዝቦች መካከል አንዱ ነው።የጋሞ አባቶች ይህን ሃሳብ ሲገልጹ ጋሞ ከጥንት ጀምሮ እንሰትን በማላመድ ሲጠቀም የኖረ ብቻ ሳይሆን ብዙ እንሰት መትከሉ በማህበረሰቡ ያለውን ከበሬታ Uuththa Haaridai dure (እንሰት ያለው ብዙ ፀጋ አለው) በማለት ይገልፃሉ። ከእርሻ በተጨማሪ የተለያዩ የሙያ መስኮች ከጥንት ጀምሮ የተሰማራ ስለመሆኑና በተለይም በሽመና (በተለይ በዶርዜ አካባቢ) ስለመሆኑ ነቃሽ የሚጠይቅ ጉዳይ አይደለም።

ከላይ እንደተጠቀሰው ጋሞ ከጥንት ጀምሮ የራሳቸው አገረሰባዊ እምነት ያላቸው ሲሆን በአንድ መለኮታዊ ሀይል፤ የማይታይና የማይዳሰስ አምላክ(ፆሳ)ና መናፍስቶች (የዘር ሐረግና የተፈጥሮ መናፍስቶች) እንዳሉና እምነታቸውም በዚሁ እንደተቃኘ ያምናሉ። ይህም አንድ ሰው መልካም ነገር እንዲገጥመው፤ ዘመኑ የሰላምና የጥጋብ እንዲሆን ትውልድ እንዲቀጥል፤ ከብቶች እንዲራቡ፤ በአገሩ ድርቅ እንዳይከሰት ዝናብ እንዲዘንብ ባጠቃለይ ጥሩ ነገር እንዲገጥመው መጥፎው እንዲርቅለት በዱቡሻ ላይ በመቆም ፈጣሪ አምላካቸው ይለምናሉ፤ ተብሎ ይታመናል።

ከላይ እንደተጠቀሰው የጎሜ ሥርዓት የጋሞ አገረሰባዊ ዕምነት አካል ሲሆን በስርአቱ የራሱ የሆኑ ክልከላዎች ያሉት ነው። እነዚህን ክልከላዎች መተላለፍ በራሱ ጎሜ (ሀጢያት) ተደርጎ የሚወሰድ በመሆኑ ይህም የፈጣሪ ቁጣ ያስከትላል ተብሎ ስለሚታመንና የፈጣሪ ቁጣም፡ ህዝቡን ለአደጋ ያጋልጣል ስለሚባል በእምነቱ መሰረት ስርአቱን የተላለፈን የማንጻት ስርዓት እንዲፈፅም ይገደዳል በማለት ይገልጻሉ። ምንም እንኳን የጋሞ አገረሰባዊ ባህልና ስርአት ጠንካራ ቢሆንም ከአስራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ወደ አካባቢው የገባው የክርስትና እምነት መስፋፋትና በቅርብ ጊዜ የመጣው የከተሜነት ዝማኔና የከተሞች

መስፋፋት በጋሞ አገረሰባዊ ስርአት ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተጽዕኗቸው እየበረታና ከጊዜ ወደ ጊዜ ዕሴቱ እየተሸረሸረ እንደሚገኝ መረጃ ሰጪዎች በአፅንዖት ይገልጻሉ፡፡

## የጋሞ ዱቡሻ ዎጋ ምንነት

ስለዱቡሻ ዎጋ ምንነትና አጀማመር የማህበረሰቡን ዕይታ ለመረዳት ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው የጋሞ አባቶች ሲያስረዱ ዱቡሻ ከጥንት ጀምሮ የነበረና ‹‹ፈጣሪ ምድርና ሰማይን ሲፈጥር አብሮ የፈጠረውና ህግ ያወረደበት "ቅዱስ ስፍራ›› ስለመሆኑ ሲያስረዱ

> «Sireppe nu nuuna ayssiza wogay nuus baawwaa. Bolan gidiri Xoossi nu wogaa dhayidi kaccishin nuuna hachi giiri be7ires. Be7irinne Hayssa deraa tumara ayssiza xillo Wogaa immana besseesi gires. Gira mala hayssa nu Dere Wogaa giza Wogaa DereDubbushshan wothis. He wodaappe doomiri hachchi gakkanaw nu siiqo! Siiqotethan merinaw daanaa**!** **...**»

አቻ ትርጉም

> …ጥንት የምንተዳደርበት ህግ አለነበረንም፡፡እግዜር ከሰማይ ላይ ሆኖ ሲመለከት … መረን ለቀን ስንደባደብ፤ ስንጣላ በትዝብት ዓይን ተመለከተን፡፡ከዚያም ፈጣሪ ‹‹ለዚህ ህዝብ የሚተዳደርበትን እውነተኛ ህግና ደንብ መስጠት አለብኝ›› … ባለውም መሰረት ይህን ዱቡሻ ዎጋ የምንለውን ህግና ደንብ በዱቡሻ ላይ አወረደልን… ከዚያ ወዲህ እስከዛሬ ስምም ነን፡፡ ስምም እንደሆንን በሰላም ለዘላለም እንኖራልን (የጋሞ አባቶች፤ ተመስገን፣ 2009)፡፡

በማለት የዱቡሻን ቀደምትነትና ዱቡሻ ለጋሞ ከዕምነት ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ ያስረዳሉ፡፡

ዱቡሻ በጋሞ የህዝብ መሰብሰቢያ አደባባይ አድረገው የሚገልጹም አሉ፡፡በዚህ አገላለጽ መሠረት እያዳንዱ የጋሞ ደሬ እንደ ጥንቱ የግሪክ ህዝብ በራሳቸው ጉዳይ ህዝቡ የሚሰበሰብበትና በነጻ የሚሳተፍበት ብሎም ስብሰባ (ዱላታ) የሚያካሄድበት በወሳኝ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚሰጡበት አደባባያቸው ነው ዱቡሻ፡፡

የጋሞ ዱቡሻ እንደ አንድ ባህላዊ መልካምድር (Cultural Landscape) መውሰድ ይቻላል፡፡ ይህን ስንል በዱቡሻ ላይ በርካታ ማህበራዊ ክዋኔዎች የሚፈፀምበት ነው፡፡ ለአብነት ዱቡሻ አዲስ የተሾሙ ባህላዊ መሪዎች ስልጣናቸው የሚፀናበት ነው፡፡ ዱቡሻ አዲስ የተጋቡ ሙሽሮች ወደህዝቡ የሚተዋወቁበት (ሶፌ የሚወጡበት)፤

ወጣቶች ከአባቶቻቸው የሚማሩበት፤ መስቀል የሚከበርበት፣ የግርዘት ሥርዓት የሚከወንበትና ሌሎች በርካታ ህዝባዊ ክዋኔዎች የሚከወኑበት ሰፊ አደባባይ ሲሆን በአጠቃላይ ህዝቡ ችግሩንም ሆነ ደስታዉንም በጋራ የሚጋራበት እንደየቦታው ትላልቅ ዛፎችና ሰፊ ሜዳ ያለበት ነው። ሌላው ዱቡሻ ከሌሎች ቦታዎች የሚለየው ልክ እንደዘመናዊው ፓርላማ ወንበሮች የተስተካከሉና ህዝቡ በየጎሳቸውና በፖለቲካ ሥልጣናቸው መሰረት የሚቀመጡበት የድንጋይ መቀመጫ ያለበት ሲሆን ሜዳው እንደተከበረ የሚወሰድ ብሎም ‹ቅዱስ› ተደርጎ ስለሚወሰድ የማይታረስ ቦታ እንደሆነ በርካታ መረጃዎች ያስረዳሉ (Bureau 1981; Freeman, 2004; ምልከታ በአጥኚዎች 2016)።




ስዕል.3

የካምባ ዱቡሻ፤ የቦንኬ ገዜሶ ዳዳ አርሼ ዱቡሻ፤ እና የደጋ ኡሞ ዱቡሻ (በሰዒድ 2016)

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ጋሞ ዕርጥብ ሳር በጥሶ ሰላም ማውረዱ ዱቡሻ በጋሞ ማህበረሰብ ያለውን እሳቤ፤ አረዳድና አተገባበር ጥልቅ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።እነዚህ እሳቤዎች ከምንም በላይ የጋሞ ህዝብ

ከሌላው በተለየ ያለውን ነባር አገር በቀል ዕውቀትና ስርዓት አሁን ድረስ የሚተገብር ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ያላቸውን ዘመን ተሻጋሪ እሴቶቻቸውንና እውቀታቸውን መጠቀም ቢችሉ ሀገራችን ኢትዮጵያ ምን ያህል ተጠቃሚ ልትሆን እንደምትችል ማሳያ ሊሆን ይችላል።



ስዕል.4
ኤሊ ዱቡሻ (በሰዒድ 2016)

በጋሞ ከአርባ በላይ የሚደርሱ ደሬዎች ያሉ ሲሆን በሁሉም አካባቢዎች ስለ ዱቡሻ ያላቸው እሳቤ፤ ትንታኔና አተገባበር ጥልቅ የሆነ፤ ጠንካራና መጤ የባህል ወረራ  እምብዛም ሊበግረው ያልቻለና በፅኑ መሰረት ላይ የፀናና የሚደነቅ አገር በቀል ተቋም/ስርዓት ነው። ለምሳሌ በቆጎታ አንድ ሽማግሌ ሲገልፁ ‹‹ዱቡሻ ለጋሞ ህዝብ ዋና አድባር ነው። ዱቡሻ እውነት የሚነገርበት፤ ሐሰት የማይነገርበት፤ ጥፋትን የሚያምኑበት፤ መርቆና ረግሞ የሚያደርሱበት ከጥንት ከቅድመ አያት ሰማይና ምድር ከተፈጠረበት ጊዜ አንስቶ … እየተከበረ ያለ  “ቅዱስ በታ ነው›› በማለት አስረድተዋል።

በቁጫ ቃለ መጠየቅ የተደረገላቸው የአካባቢ ሽማግሌዎች ሲገልጹ፡-

> … ዱቡሻ ከአያት ቅድመ አያት በውርስ የመጣ የዛሬይቱ አትዮጵያ አንድ ከመሆኗ በፊት፤ እያንዳንዱ ማህበረሰብ ለብቻው በሚኖርበት ዘመን፤ በጋሞ የነበረ እውነተኛ መንገድን የሚያስተምር ህዝብ ተሰብስቦ በጋራ የሚነጋገሩበትና የሚወስኑበት ማስረጃ ሳያስፈልግ እውነት የሚወጣበት፤ …ያለ ልዩነት እውነተኛ ፍትህ የሚሰጥበት የእውነትና የፍትህ አደባባይ ነው። በተጨማሪም ዱቡሻ ጎሳን ከጎሳ፤ ዴሬን

> ከዴሬ ጋር የሚያስተሳሰር በመካከላቸው መተማመን የሚፈጥርና አንድነታቸውን የሚሸምን የዕውነት ድርና ማግ ነው።ዱቡሻ ለጋሞ የዕውነት መገለጫ ነው።ዱቡሻ ለጋሞ ህዝብ እምነቱ ነው። የጋሞ ህዝብ በሰማይ እግዚአብሄርን በምድር ዱቡሻን ይፈራል...

በማለት የማህበረሰቡን እሳቤ አስረድተዋል።

በተጨማሪም ዱቡሻ ‹‹የጫቆ (መሀላ) ቦታ ነው። እውነትና ዉሸት የሚለይበት፤ የምርቃት ቦታ በመሆኑ የተቸገረ በረከትን የሚቀበልበት፣ ፍትህ የሚሰጥበት፤ የማይታረስ፤ የተከበረና የተፈራ ‹ቅዱስ› የሆነ የመሃላ ቦታ ነው›› በማለት ከበረዳ ቃለ መጠየቅ የተደረገላቸው የአካባቢ ሽማግሌዎች ገልጸዋል። በተመሳሳይ ጋርዳ ማርታ ቃለ መጠየቅ የተደረገላቸው የአካባቢው ሽማግሌዎች ሲያብራሩ “ዱቡሻ እጅግ የሚከበርና የሚፈራ የፍትህና የእውነት ቦታ ሲሆን በዱቡሻ ላይ የሚደበቅ ምንም ነገር የለም” በማለት አስረድተዋል።

እንደዚሁም በቦንኬ ገዘሶ ከተማ ቃለ መጠየቅ የተደረገላቸው የአካባቢው ሽማግሌዎች ዱቡሻ “ከጥንት ከቅድመ አያቶቻችን ዘመን ጀምሮ የነበረ ዛሬ በኛ ዘመንም ያለ፤ የተደበቀንና ማስረጃ ያልተገኘበትን ጉዳይ እውነቱን በአደባባይ እንዲወጣ የሚያደርግ የጋሞ መተዳደሪያ ስርአት ሲሆን ጋሞና ዱቡሻ በታሪክ የተቆራኙ ናቸው። ጋሞ ችግርን የመፍታት እሴት ያጎለበተው ቅዱስ በሆነው በዱቡሻ ላይ በመሆኑ ዱቡሻ የጋሞ ህልውና ነው።” በማለት አስረድተዋል።

እዚህ ላይ ከላይ የተዘረዘሩትን እሳቤዎች ጠቅለል አድርገን ስንመለከታቸው ዱቡሻ ለጋሞ የእውነትና የእኩልነት ብሎም የፍትህ አደባባይ ከመሆኑም በላይ ፈርጀ ብዙ ማህበራዊ ክዋኔዎች የሚከወኑበት፤ ለወጣቱ የጋሞን እሴት መማሪያ፤ አለምን የሚያይበት የእምነትና የፍልስፍና መተዳደሪያ ህግና ደንብ የሚወጣበትና የሚተረጉምበት ባህሉንና ታሪኩን ለሚቀጥለው ትውልድ የሚያስተላልፍበት ታላቅ ተቋም/ስርዓት እንደሆነ መረዳት አያዳግትም። ይህም በማህበረሰቡ የተለየና ሁሉን አቀፍ ቅቡልነት ያለው፤ የሚከበርና የሚፈራ ‹ቅዱስ› ተደርጎ የሚወሰድ በመሆኑ ዱቡሻ ዎጋ የጋሞን አንድነት የሚያሳይ ድንቅ ከሆኑ የአገር በቀል እሴቶች ዋናው አድርጎ መውሰድ ይቻላል።

በቦንኬ ገዘሶ ላይ አንድ የጋሞ አባት ዱቡሻን ሲገልፁ “ለጋሞ ዱቡሻ እናት እንደ ማለት ነው። የጋሞ ብሔረሰብ በውስጡ ብዙ ዴሬዎች አሉ። አንድ የሚያደርጋቸዉ ግን የዱቡሻዉ ሥርዓት ነዉ። በዱቡሻ የሰው ልጅ እኩል

ነው። በዱቡሻ የዘር፤ ሃይማኖት የጾታ ወዘተ ልዩነት የማይታይበት ሁሉም በእኩልነት ልክ እንደ እናት ደስታውንም ሆነ ችግሩን የሚጋራበትና ሁሉንም እኩል አቅፎ የያዘ ባይራ (ቀዳማይ) ባህል ነው” ብለዋል።

በአትኩሮት የቡድን ወይይት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለከተው ከሆነ ዱቡሻ የጋሞ ህልውና ስለመሆኑ ሲያብራሩ “ህዝብ ያለ መሪ መኖር እንደማይችል ጋሞ ያለ ዱቡሻ መኖር” እንደማይችል ተሳታፊዎች ገልጸዋል፡፡ ለጋሞ ዱቡሻ የመጀመሪያ ባህላዊ ተቋም ሲሆን ለክፉም ለደጉም ውሳኔ የሚሰጠው በዱቡሻ ነው። “ከፈጣሪ በታች ጋሞ በዱቡሻ ያምናል” ማለት ሐሳባቸውን አጋርተዋል።

በተጨማሪም የጋሞ ህዝብ የሚተዳድርባቸው በርካታ ዎጎች (ስርአቶች/ህጎች) የሚወጡትና የሚተገበሩት ህዝብ በተሰበሰበበት ትልቅ የዱቡሻ አደባባይ ላይ ነው።እነዚህ ዎጎች ቤተሰብን ከቤተሰብ፤ ጎሳን ከጎሳ፤ ህዝብን ከህዝብ የሚያስተሳሰሩና የሚጠብቁ፤ የህዝቡን መተማመንና አንድነትን የሚያረጋግጡ፤ ፖለቲካዊ፤ ማህበራዊ፤ ባህላዊ እና እኮኖሚያዊ ጉዳዮችን እንዲሁም ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ጉዳዮችን የሚያስተዳድሩ ናቸው። በዱቡሻ ላይ በርካታ ህጎች የሚወጡና የሚተገበሩ ህጎች ሲሆን ለአብነት ያህል የመሬት ህግ፣ “የቅዱስ ስፍራዎች” ህግ፣ የአስተዳደር ህግ፣ የምርቃት ህግ፣ የእርግማን ህግ፣ የጋብቻ ህግ፣ የሰም አወጣጥ ህግ፣ የለቅሶ ህግ፣ የውርስ ህግ በጥቂቱ መግለጽ ይቻላል።[8] በመሆኑም ዱቡሻን ልክ እንደዘመናዊዉ የጋሞ የህዝብ ምክር ቤት አድርጎ መውሰድ ሲቻል ህጎች የሚወጡበትና የሚጸድቁበት፤የህዝቡ አንድነት የሚጠበቅበት፤ ችግሮች በዉይይት የሚፈቱበት፤ መተማመን የሚፈጠርበት በመሆኑ ዱቡሻ የጋሞ አንድነት መገለጫ ብቻ ሳይሆን የጋሞ አንድነት የቆመበት መሰረት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። ስለሆነም የዚህ ፅኁፍ ዋነኛ ማተኮሪያ የዱቡሻ ዎጋ ለዘላቂ ሰላም ያለዉን ሚና ከዚህ በታች ለማቅረብ ተሞክሯል።

**ዱቡሻ ዎጋ ለዘላቂ ለሰላም ያለው ፋይዳ**

ዱቡሻ ዎጋ ለዘላቂ ሰላም ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ስለመሆኑ መረጃ ሰጪዎች ሲገልፁ በዱቡሻ የሚፈቱ ግጭቶችና አለመግባባቶች በማያጠራጥር ሁኔታ ቂም በቀልን ከስሩ በማድረቅ፤ ቁርሾዎችን ከልብ (qanthappe) በመፍታት የተራራቁትን በማቀራረብ (Iginthon, Dabbothon, Maqyinthon) በዘላቂነት ህብረተሰቡ አንድ


[8] እነዚህ ህጎች የጋሞ አባቶችና አዋቂዎች በራሳቸው ባህል መሰረትና በሁኔታዎች ኑባሬዎች መሰረት ህግ ያወጣሉ። ይተገብራሉም።

እንዲሆን የማድረግ ሚናውን ከፍተኛ ነው በማለት ያስረዳሉ። እንደሚታወቀው በሰላም ግንባታ ሂደት እውነትና ፍትህ ለዘላቂ ሰላም ዋና ዋና ምሰሶዎች ናቸው።

ዱቡሻ የእውነትና የፍትህ አደባባይ በመሆኑ ችግሮችን በዘላቂነት በመፍታት አቻ የለሽ ተቋም ነው። ዱቡሻ የዕምነትና የመሀላ (C'aaqo/ qangetha) አደባባይ በመሆኑ በህብረተሰቡ ያለው ቅቡልነቱ የላቀ ነው። በአትኩሮት ቡድን ውይይት ላይ የተሳተፉ ሰዎች እንደገለጹት ከሆነ ዱቡሻ እኩልነት የሚረጋግጥበት መድረክም ነው። በዱቡሻ ሀብታም፣ ድሃ፣ ወንድ ሴት፣ ልጅ አዋቂ፣ መጤ፣ ነባር የሚባል ክፍፍል ቦታ የላቸውም። ዱቡሻ ለሁሉም እኩል ፍርድ የሚሰጥበት የጋሞ ባህላዊ ፍርድ ቤት እንደማለት ነው። በተጨማሪ በዱቡሻ ላይ ያለው ሥርዓትና አሰራር ከአድሏዊ አሰራርና ከዕጅ መንሻ የፀዳ በመሆኑ ፍርደ-ገምድልነት በዱቡሻ ቦታ የላቸውም፤ አይታስብምም። ምክንያቱም ድርጊቱ የፈጣሪን ቁጣ/መቅሰፍት (ጎሜ) ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ስለሚታመንና በዱቡሻ ላይ የዋሸ ሰው ጎሜ ይገጥመዋል ተብሎ ስለሚታመን ዱቡሻ ላይ የቆመ ዳኛም ሆነ በዳይ ውሸት ከመናገር ይቆጠባሉ። ማስረጃ ያልተገኘለት ጉዳይም ያለ ማንም ጫና እውነቱን በመናገር ከፈጸመው በደል ተፀፅቶ እንዲናገር ይደረጋል። ይህም ዱቡሻ ላይ ፈጣሪ እውነት ብቻ እንዲነገር የመረጠው ቅዱስ ቦታ ከመሆኑም ባሻገር ፈጣሪ ለጋሞ ካበረከተው ነገሮች አንዱ ዱቡሻ ነው ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ በጥናቱ ላይ ቃለ መጠየቅ የተደረገላቸው ሰዎች አስረድተዋል።

ጋሞ ችግሮች ሲፈጠሩ ችግሮችን የሚፈቱትና ሰላማቸውን የሚያፀኑት የዱቡሻ ዎጋ ስርአትና መዋቅራዊ አደረጃጀቱ በጠበቀ መልኩ እንደሆነ ያስረዳሉ። በጋሞ ሶስት አይነት/ደረጃ ያላቸው ዱቡሻዎች ሲኖሩ የመጀመሪያው የዳበ(የጎሳ) ዱቡሻ ሲሆን የቤተሰብንና የጎሳን ጉዳዮች የተመለከቱ ቀለል ያሉ ጉዳዮች ይመለከታል። ሁለተኛው የጉታ (የመንደር) ዱቡሻ ሲሆን የመንደርን፤ የእርሻ ድንበርንና ሌሎች መለስተኛ ጉዳዮች ለመዳኘት የተደራጀ ሲሆን፤ ሶስተኛውና ትልቁ ደሬ ዱቡሻ ደግሞ ቀበሌ ከቀበሌን፤ ዴሬ ከዴሬ የተገናኙና ትልልቅ ህብረተሰብ አቀፍ ጉዳዮች የሚታዩበት ነው እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ያስረዳሉ። በሂደቱም በዝቅተኛው ደረጃ በታየ ጉዳይ ቅር የተሰኘ የዱቡሻ መዋቅራዊ አደረጃጀትን ተከትሎ ከቤተሰብ ጀምሮ በመንደር ብሎም ከፍ ብሎ ይገባኛ በመጠየቅ እስከ ዴሬ ዱቡሻ በማድረስ ፍትህና ርትዕን እንዲከበር ይደረጋል ሲሉ መረጃ ሰጪዎች ያስረዳሉ። ስለሆነም ችግሮችን ደረጃ በደረጃ ከታች ወደላይ ሂደታቸውን ጠብቀው መፈታት መቻላቸው ዱቡሻ ዎጋ በጋሞ ማህበረሰብ ዘንድ ያለውን ጠንካራና ዘመን ተሻጋሪ

ተቋምነት ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ባጠቃለይ ዱቡሻ ካለው የራሱ የሆነ መዋቅራዊ አደረጃጀት፤ ቅቡልነትና ችግሮችን ቀድሞ በመከላከልና ችግሮች ሲፈጠሩም ከስራቸው በመፍታት ጋሞ ከጥንት ጀምሮ ዘላቂ ሰላም በመገንባት መኖር መረጃ ሰጪዎች ያስረዳሉ።




ስዕል.5

የጋሞ ዱቡሻ መዋቅራዊ አደረጃት (ከመስክ ዳሰሳ የተወሰደ)

ከላይ የተመለከተው የዱቡሻ አወቃቀር ከጋሞ አሰፋፈርና ጥንታዊ አስተዳደር ሥርዓት ጋር ቀጥታ ግኙኑነት እንዳለው መረጃ ሰጪዎች ይገልፃሉ።ይህንንም ፈረንሳዊ አንትሮፖሎጀስት ጃክ ባወሩ ሲገልጽ አንድ ሰው በጋሞ ውስጥ አባልነቱ በቤተሰብ ውስጥ ቀጥሎ በጎሳ ቀጥሎ በጉታ (በመንደር) በመጨረሻም በዴሬ መሆኑን “Dere is made up of several neighborhoods (Gutata). The neighborhood is a community of several households (ketseta)-these are organized around the head of the household: the father(ade) or when he dies his eldest son (Baira) (Bauer 1981፡34) በማለት ይገልፃል። በአንድ ዴሬ ውስጥ በርካታ ጉታዎች (neighborhoods) አንድ ላይ “ፌደሬሽን” ይመሰርታሉ። ይህም ከአርባ በላይ በሆኑ የጋሞ ደሬዎች አሰፋፈርና አደረጃጀት ላይ የተመሰረተ ነው ሲል አጥኚው ይገልጻል። በመሆኑም ግጭቶችና አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በሁለት መንገድ ይፈታሉ። አንደኛው በዴሬ ውስጥ ሲሆን ይህም በቤተሰብ ብሎም በጉታ እና በመጨረሻም በዴሬ እንደየችግሩ ግዝፈት የሚፈታበትና ዘላቂ ሰላም የሚፀናበትና ስብራት

የሚጠገንበት ሲሆን ሁለተኛው በደሬዎች መካከል የሚደረግ የግጭት አፈታትና ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን የሚደረግበት ሂደት ነው።

የዱቡሻ ስርአትንና ክዋኔ በሁሉም ዴሬዎች ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ በአንዱ ዴሬ ያጠፋ ወደ ሌላኛው ዴሬ ሸሽቶ መደበቅ ስለማይችልና ከአንዱ ጉታ ወደ ሌላ ጉታ እንዲሁም ከአንዱ ዴሬ ወደ ሌላ ዴሬ የሚሄድ ሰው በወንጀል ከተጠረጠረና ወደነበረበት ተመልሶ ዱቡሻ ላይ እንዲታይ ይደረጋል። በዱቡሻ ወግና ሥርዓት ነጻ መሆኑ ተረጋግጦ ሊሄድ ይችላል። በመሆኑም ዱቡሻ ቤተሰብን ከቤተሰብ ጉታን ከጉታ ብሎም ዴሬን ከዴሬ ጋር በማቀራረብ የአጠቃላይ ጋሞ አንድነትና ሰላም እንዲጠበቅ ከማድረግ አኳያ የሚጫውተው ሚና ከፍተኛ ነው።

ለዚህ ሐሳብ እንደማሳያና ንጥል ጥናት ሊወሰድ የሚችለው መረጃ በምንሰበስብበት ጊዜ በዳራ ማሎ ጮዬ ሶዶ ዴሬ በግለሰቦች መካከል የተፈጠረ ግጭት ወደ ጎሳ ብሎም ወደ ቀበሌ (ጉታ) አድጎ የአካባቢው መንግስት ሰላም ለማስፈን ተቸግሮ ጉዳዩን ወደዱቡሻ በማምጣት ከስምንት ወራት በኋላ በጮዬ ዱቡሻ የተፈታበትን የእርቅ ሥርዓት ለመታደም እድል አግኝተን ነበር። ከአካባቢው የእርቅ ሥርኣቱን ከሚያስፈጽሙት የዱቡሻ መሪዎች ያገኘነውን መረጃ እንደሚከተለው እናቀርባለን።

ችግሩ የተፈጠረው በግለሰብ ደረጃ ሲሆን እያደር ወደ ቀበሌ ያደገና የሚመለከተው አካል ለመፍታት ያስቸገረ ግጭት ሲሆን በመጨረሻም የጋሞ አባቶች በአጭር ጊዜ ሁለቱንም ወገኖች ፊት ለፊት በማገናኘት የፈቱበትና ቂም በቀልን ከስሩ ያደረቁበት በዳይም በራሱ ጊዜ በአደባባይ ራሱን ጥፋተኛ ያደረገበት ሁኔታ ለመታዘብ ችለናል። ጉዳዩ እንደ መረጃ ሰጪዎች አባባል ከሰኔ 2015 እስከ የካቲት 2016 ዓ.ም የቆየ ሲሆን የተጀመረውም በሚከተለው ሁኔታ ነው።

> ...ከሜዜ ገበያ የሚመጣ የሌጼ ቀበሌ ነዋሪ አንድ ወጣት ባልታወቀ ምክንያት ህይወቱ ያልፋል። ሁለቱ ቀበሌዎች የሶዶ ዴሬ አካል ናቸው። በዕለቱ የሟች ቤተሰብ የበቀል ርምጃ ለመውሰድ ይሄዳሉ፡ ፡ በሄዱበት ሌላ ግጭት ይፈጠርና በድጋሜ ከሁለቱም ወገኖች ተጨማሪ … አደጋ ይከሰታል። ይባስ ብሎ በሁለቱም ወገኖች ላይ በርካታ የንብረት መውደም፤ የቤቶች መቃጠልና የህዝብ መፈናቀል ይከሰታል። ጉዳዩም ከቁጥጥር ወጥቶ የሚመለከተው አካል ሰላም ለማስፈን ትልቅ ተግዳሮት

ገጥሞት ነበር። ይህንን ከባድ አደጋ ለዕምነታቸውና ለባህላቸው ቀናኢ የሆኑ ከሌላ ዴሬ የመጡ[9] የጋሞ አባቶች ‹‹እኛ እያለን ዱቡሻ እያለ ጨዬ ተበድለሃል! ጉዳይህን ጨዬ ዱቡሻ ላይ እናያለን! ዉጣ በማለት ተሰበሰብን…



ስዕል.5 በጨዬ ደሬ የተካሄደ የግጭት አፈታት ስርዓት (በሻ 2016ዓ.ም)

በማለት ሁለቱንም ወገኖች በዱቡሻ ወግና ስርኣት ግጭቱን መፍታት ብቻ ሳይሆን ቂም በቀልን በማድረቅ የተበደለን በመካስ ጥፋተኛን ለሚመለከተው የህግ አካል አሳልፈው ሲሰጡ ጥፋተኛውም በራሱ ጥፋተኛነቱን አምኖና በራሱና ብሎም በቤተሰቡ ከሚደርስበት ጎሜ ለመንጻት ራሱን ለህግ ተጠያቂ በማድረግ ወደሚመለከተው አካል ተላልፎና በህግ ተጠያቂ መሆን የቻለበትን ሁኔታ በጨዬ ዱቡሻ ላይ በአይናችን ለመመልከት ችለናል። ይህም የጋሞ ዱቡሻ ዎጋ በጋሞ ማህበረሰብ ዘንድ ያለውን ቅቡልነት ብሎም ለዘመናዊ የፍትህ ስርአት ከማገዙም በላይ በዳይ ካለምንም ጫናና ግፊት በራሱ አምኖና ተፀፅቶ ሊደርስ ከሚችል ማህበረሰባዊ ቀውስ ራሱን የመፍትሄ አካል በማድረግ በህብረተሰቡ ዘንድ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን አይነተኛ ሚና ሊጫወት እንደተቻለ ለመገንዘብ ይረዳል።

[9] አንዳንድ ጉዳዮችን በተለይም በዴሬና ደሬ ሲፈጠሩ፤ በጉታዎች መካከል የተፈጠረን ህዝባዊ ግጭት የእርቅ ሂደቱን ለማስኬድ ከሌላ ዴሬ የመጡ የጋሞ አባቶች ቀን ቆርጠው በራሳቸው ሄደው እንደሚፈቱ ተነግሮናል። ይህም ከጉዳዩ ጋር ገለልተኛ የሆኑትንና አድሏዊነትን ለማስቀረትና ሁሉም ዴሬዎች ጉዳዩ ስለሚመለከታቸው በቅንነት ለማሳተፍ በሚል እንደሆነ ተነግሮናል፡ ፡

**ማጠቃለያ**

ከላይ ከቀረበው ጥናት መረዳት እንደሚቻለው ዱቡሻ ዎጋና ሌሎች ተመሳሳይ አገር በቀል ዕሴቶች በማኅበረሰቡ ዘንድ ባላቸው ቅቡልነት በየጊዜው የሚፈጠሩ ችግሮችን በአጭር ጊዜና ያለምንም ወጪ መፍታት መቻላቸው ብቻ ሳይሆን ለአላስፈላጊ ብክነት ሳይጋለጡ ዘላቂ እልባት እየሰጡና ቂምና ቁርሾን በማጥፋት ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን በማድረግ ላይ አይነተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ። ለአብነት በዱቡሻ ላይ የሚፈቱ ግጭቶች ዘርፈ ብዙ ፋይዳ እንዳላቸው በጥናቱ ላይ የተሳተፉ ቃለ መጠየቅ የተደረገላቸው ሰዎች ሲገልጹ ግጭቶችን ማህበረሰቡ በፈጠራቸው በራሱ ተቋም መፍታት ከማህበረሰቡ ስነልቦና፤ ባህል፣ ወግና ልማድ መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው ለዘላቂ ሰላም ማህበራዊ ፋይዳቸው እጅግ የጎላ እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

እንደማንኛውም ማህበረሰብ ጋሞ በተለያዩ መልከአምድረ የሰፈረ ቢሆንም ህብረሰተሰቡ በለቅሶ፣ በሰርግ፣ በገበያ፣ በደቦ እና በመሳሰሉ ማህበራዊ ክንዋኔዎች እለት ተእለት ይገናኛል። በእነዚህ ግንኙነቶች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች ቀደም ሲል የነበረውን ማህበራዊ መስተጋብሮችና ግንኙነቶች እንዳይታወኩና ወደነበሩበት እንዲመለሱ የዱቡሻ ሽማግሌዎች ጉዳዩን በዱቡሻ በዎጋ ስርአት ተጠንቅቀው ይፈጽማሉ። የእርቅ ሥርዓቱም ቁርሾን ከሥሩ በመንቀል እንዲታረቁ ስለሚያደርግ ለማህበረሰቡ ሰላማዊ ኑሮና መተሳሰር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው።

የዱቡሻ ዎጋ ግጭት አፈታትን ከፍርድ ቤቶች ጋር ስናነጻጸር ፍ/ቤቶች በተቀመጠላቸው ህግና በማስረጃ ላይ ብቻ ተመሥርተው ስለሚፈርዱ ፍርዱ ጥፋተኛውን ተጠያቂ ከማድረግ ዉጪ ቀጣይ ማህበረሰባዊ ግንኙነቶችን ብሎም ቂምበቀልም ለመከላከል ብሎም አላስፈላጊ ቀጣይ ጥፋቶች እንዳይከሰቱ ከማድረግ አኳያ የራሱ የሆነ ዉስንነት እንዳለበት መረጃ ሰጪዎች ያስረዳሉ። በሌላ በኩል ግጭቶች በድቡሻና ሌሎች አገርበቀል ስርኣቶች መፍታት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ብቻ ሳይሆን ዘላቂ ሰላምና የማህበረሰብን ቁርኝት ማጥበቅ ሚናቸው የጎላ እንደሆነ ያስረዳሉ። ቃለ መጠየቅ የተደረገላቸው ሰዎች ሲያስረዱ በዱቡሻና በመሰል ተቋማት ግጭቶች የሚፈቱ ከሆነ ችግሮቹ የፈለገውን ያህል ውስብስብና አስቸጋሪ ቢሆኑም በአጭር ጊዜ በፍትህ እንዲያልቁና ጥፋተኛውን ለሚመለከተው አካል ለማድረስ የሚከተሉትና የሚያደረጉት ባህላዊ ስርኣት ሁለቱም ወገኖች በነዚህ ስፍራዎች ሲቆሙ ያለማንም ጣልቃ ገብነት ፈጣሪቸውን በመፍራትና

በመጸጸት እውነትንና እውነትን ብቻ እንደሚናገሩና እንደሚያምኑ ያስረዳሉ፡፡ ይህም ግጭቶችን በአጠረ ጊዜ ስለሚፈቱ ሁለቱ ወገኖች ጊዜያቸውን ለምርታማ ሥራ እንዲያዉሉና ይረዳቸዋል፡፡ይህም ግጭቶችን በዱቡሻ መፍታት ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በተቻለ መጠን ዱቡሻና መሰል የአገርበቀል ተቋማት ካለባቸው ዉስንነት አንጻር ከዘመናዊ አሰራር ጋር ቢቆራኙ እጅግ የተሻለ ዉጤት ሊገኝ ይችላል ብለው መረጃ ሰጪዎች ምክረ ሀሳባቸውን ያቀርባሉ፡፡

በተጨማሪም ግጭቶችን በዱቡሻ ዎጋና መሰል አገር በቀል ስርዓቶች መፍታት መቻል ፖለቲካዊ ፋይዳቸውም የጎላ ይሆናል፡፡ ይኸውም በማንኛውም ህብረተሰብ ውስጥ የሚገነባ የፖለቲካ ሥርዓት ዋና ዓላማ ሥልጣኑን በያዘው መንግሥት አማካይነት ከማንኛውም ጉዳይ አስቀድሞ የሚመራውን ህዝብ ፍላጎትና ጥቅም ማስከበርና ዘላቂ ሰላምንና ደህንነቱን ማስጠበቅ ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ ህብረተሰቡ የሚገኝበትን ነባራዊ ሁኔታ ባህሉን፣ ወጉንና ልምዱን ያገናዘበ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና የፍትህ ሥርዓት መዘርጋትን ግድ ይለዋል፡፡ ይህም በአገራችን ጠንካራ የፖለቲካ ሥርዓት እንዲፈጠር ሚናው የጎላ ነው፡፡

በአጠቃላይ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍንና ግጭቶችን ቀድሞ ከመከላከል አንፃር የዱቡሻ ዎጋና በመሰል ተቋማትን በማጠናከርና ከዘመናዊ አሰራር ጋር ማቀናጀት ቢቻል በማህበረሰቡ መካከል የሚፈጠሩ ቁርሳችን በማስወገድ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትና ሰላም ዘላቂ እንዲሰፍን ያስችላል፡፡ ዘላቂ ሰላም ለሁሉም ነገር መሰረት ሲሆን በግጭቱ ምክንያት የሚፈጠር ስጋትን በመቀነስ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትን በማጠናከር ሀብትን ለአገር ልማትና ብልፅግና ማዋል እንዲቻል ለነዚህ ተቋማት የንስር አይን ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

**ዋቢዎች**

Adam, A. H. (2012). Recognising sacred natural sites and territories in Kenya. In L. Maffi, O. Dilts, B.Verschuuren, & R. Wild (eds.), Sacred Natural Sites; Sources of Biocultural Diversity (pp.20-23). Salt Spring City: Langscape. Terralingua

Booker, S., & Shrumm, H. (2012).Protecting the Sacred: The role community protocols play in the protection of sacred natural sites. In L. Maffi, O. Dilts, B.Verschuuren, & R. Wild (eds.), Sacred Natural Sites; Sources of Biocultural Diversity (pp.34-39). Salt Spring City: Langscape. Terralingua.

Bureau, J. (2012). *The Gamo of Ethiopia: A Study of Their Political System*. Bardwell Press.

Desalegn Desissa. (2007). The Biocultural Diversity of Living Indigenous Sacred Landscape in the Gamo Highlands of Ethiopia. Addis Ababa, Ethiopia: EWNHS.

Desalegn Desissa & Healey, J.R. (2012). Sacred groves in the Gamo Highlands of southern Ethiopia: biocultural values and threats. In L. Maffi, O. Dilts, B.Verschuuren, & R. Wild (eds.), Sacred Natural Sites; Sources of Biocultural Diversity (pp.44-47). Salt Spring City: Langscape. Terralingu

Desta Mussa. (2024). “The Effect of Development Interventions on The Sacred Areas In Gamo Highlands”. MA Theses. Arba Minch University.

Eller, J. D. (2007).Introducing Anthropology of Religion: Culture to the Ultimate. Newyork and London: Routledge.

Freeman, D. G. (1999). Transforming traditions: the dynamics of cultural variation in the Gamo Highlands, southwest Ethiopia.Dissertation. London School of Economics and Political Science, United Kingdom

Iwatsuki, K. (2003, February). Japan sacred mountains.International workshop on the importance of sacred natural sites for biodiversity conservation, Kunming and Xishuangbanna biosphere reserve.People Republic of China, February 17–20, 2003.Lee, C., & Schaaf. T (eds.). China: UNESCO (pp.89-90).

Schaaf, T. (2003).UNESCO‟s experience with the protection of sacred natural sites for biodiversity conservation. International workshop on the importance of sacred natural sites for biodiversity conservation, Kunming and Xishuangbanna biosphere reserve. People‟s Republic of China, February 17–20, 2003.Lee, C., & Schaaf. T (eds.). China: UNESCO (pp.13-20)

Tadesse Wolde. (2009). We Have Been Sold: Competing with the State and Dealing with Others. In Günther Schlee & Elizabeth E. Watson (eds.), Changing Identifications and Alliances in North-East Africa, 3 (pp.135-153). New York, Oxford: Berghahn Books Press.

Zerihun Doda. (2018). The role of sacred natural sites in conflict resolution: Lessons from the Wonsho sacred forests of Sidama, Ethiopia. SAGE Handbook of Nature, 3(1), 938- 967

ተመስገን *ምንዋጋው። (2009)።* የጎሜ ልማታዊ ገጽታ በጋሞ ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በፎክሎር ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ.